4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 30727

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አልማው ወሌ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ/ማኅበር ነ/ፈጅ ወንድአንተ ነጋሽ

ተጠሪ ፡- ጆቲቲ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ግራ ቀኞችን ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ውል ከከሳሽ ጋር 10 ኢንች የማይዝግ የብረት ቧንቧ ለማቅረብ ስምምነት የተደረሰ ቢሆንም ተከሳሽ ውሉን በማፍረሱ ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት ችግሩን ለመፍታት ከሳሽ የበኩሉን ጥረት ቢያደርግም በተከሳሽ በኩል አዎንታዊ ምላሽ ባለመገኘቱ በውሉ አንቀጽ 10/4/ /2/ መሠረት ጉዳዩን በግልግል ለማየት ተጠሪ የግልግል ዳኛ በ10 ቀን ውስጥ መርጦ እንዲያሳውቀን በጽሁፍ ያሳወቅነው ቢሆንም ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሳሽ ምትክ በሕግና በውላችን መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ አቤቱታም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በሕግም ሆነ በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ፤ በመተዳደሪያ ደንቡ እንደዚሁም በሥነ ሥርዓትና በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠው የችሎታ መስፈርት ለተጠሪው ወይንም ለእንደራሴው አልተሰጠም ብለ  ነም ሌላ ተከሳሽ የግልግል ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በእራሳቸው ችሎታ ሳይሆን በሌሎች የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰዎች ስም የሆነ እንደሆነ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ እንዲስማሙ የሚያስችላቸው ልዩ የውክልና ስልት እንዲኖራቸው ይገባል ያሉ ሲሆን አመልካች ወደ ግልግል ዳኝነት እንግባ የሚልበት ጉዳይ በግልግል ስምምነቱ አይሸፈንም እንጂ የሚሸፈን ነው ቢባል እንኳ ወደ ግልግል ዳኝነት ከመግባቱ በፊት በእራሳቸው በተዋዋዮች ድርድር ተጀምሮ በሂደት ላይ ያለው ስምምነት ገና ያልተጠናቀቀ ስለሆነና ይህንንም ለማድረግ ውሉ ስለሚያስገድድ በዚህ ሁኔታ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተገቢነት ያለውን የክርክሩን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ተጠሪ የአክሲዮን ማኀበር ሲሆን ተጠሪና አመልካች ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተዋዋሉት መሠረት ያለመግባባቶችን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ተደርጐ ካልተቻለ የግልግል ዳኛ በመምረጥ ጉዳዩ እንደሚታይ የተስማሙ ስለሆነ አክሲዮን ማኀበር ያለመግባባቶችን በግልግል ለመፍታት እንደማይችል የሚያመለክት የሕግ

ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጉዳዩን በግልግል መጨረስ አልችልም በማለት ያቀረበው ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ካለ በኋላ የተፈጠረውን ያለመግባባት በውሉ መሠረት በስምምነት ለመፍታት ከሳሽ /አመልካች/ ተገቢውን ጥረት ስለማድረጉ ካቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ግራ ቀኙ ያለመግባባታቸውን በስምምነት መጨረስ ስላልቻሉ ጉዳያቸው በግልግል ዳኛ አማካይነት መታየት ስላለበት የየበኩላቸውን የግልግል ዳኛ መርጠው ይቅረቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በግልግል ዳኛ እንዲታይ በበታች መወሰኑ አግባብነቱ ተጠሪ ባለበት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባው ( ኑጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡



የዚህን ችሎች ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው አለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

በቅድሚያም አመልካች ምን ዓይነት የሕግ ሰውነት (legal personality) እንዳለው መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ሲታይ አመልካች የአክሲዮን ማኀበር እንደሆነ ከክርክሩና ከቀረበው ማስረጃ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይህንንም የሕግ ሰውነት ማግኘት የቻለው አስቀድሞ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበረና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/91 መሠረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኀበርነት እንዲለወጥ ማድረግ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 5/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት አመልካች ወደ አክሲዮን ማኀበርነት የተቀየረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቋቋሙና በንግድ ሕጉ መሠረት የሚቋቋሙ የአክስዮን ማኀበራት በአክሲዮን ባለቤትነት በሥልጣንና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ከተጠቀሰው አዋጅ መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ የንግድ ሕግ ቁጥር 307/1/፣ 311፣ 312/1/ለ/፣ 315፣ 347/1/ እና 349 ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኀበርነት በተለወጡት ላይ ተፈፃሚነት እንደሌላቸው ነገር ግን ሌሎች የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት የአክሲዮን ማኀበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው እንደሚችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 348/3/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በተያዘውም ጉዳይ አመልካች አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለው ስለመሆኑ በአክሲዮን ማኀበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የተመ ኑን ተገንዝበናል፡፡



በሌላ በኩልም የአመልካች አክ ነበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በማኀበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆን ተጠሪም በዚሁ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12/2/ ሥር ዋና ሥራ አስኪያጁ የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራ ያከናውናል ተብሎ የተመለከተው ከሌሎች ወገኖች ጋር ውል መዋዋልን በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩን በግልግል ለማየት መስማማት እንደሚችልም ስለሚያስገነዝብ በዚሁ መሠረት ውሉ የተፈረመ ስለሆነ ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ መወሰኑ አግባብነት አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና ዋናው ሥራ አስኪያጅ የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል ተብሎ ሥልጣንና ተግባሩን በሚዘረዝረው የማኀበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም አክሲዮን ማኀበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ሲታይ ሙሉ በሙሉ በንግድ ሕጉ መሠረት ያልተቋቋመ ስለሆነና ዋናው ሥራ አስኪያጁ ኩባንያውን በመወከል ውል የመዋዋል ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ ቢቻልም ከዚህ አልፎ በውሉ አፈፃፀም

ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩ በግልግል ዳኛ አማካይነት ዕልባት እንዲያገኝ ለመስማማት እንደሚችል ሥልጣን ያልተሰጠው መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት ይችላል በማለት የሰጡት ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 146/91 እና ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 59068 በየካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 46254 በየካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተቋቋመበ ሊያና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ዋናው ሥራ አስኪያጅ በውል አፈፃፀም ረገድ የሚፈጠርን ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ዕልባት እንዲያገኝ ለመስማማት ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ አይችልም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ





# ልዩ ልዩ